# የከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና

# የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የብድር አሰጣጥ

# መመሪያ ቁጥር 1/2009

የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት
ግንቦት 2009 ዓ.ም

# የከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የብድር አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1/2009

የውሃ ልማት ፈንድ የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛዎችን በሕግ መምራት በማስፈለጉ፣ የፈንዱን የብድር አስተዳደር ሥርዓት ቀልጣፋና ለባለድርሻ አካላት ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፣ የፈንዱን የብድር አሰጣጥ ሥርዓት ፍትሐዊ እና እኩል ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣

የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 268/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 7(2) እና 14(4) ለውሃ ልማት ፈንድ ቦርድ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የብድር አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2009 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ጽ/ቤት" ማለት የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ነው።
2. "ብድር" ማለት ለከተሞች መጠጥ ውሀና ሳቴኒሽን ፕሮጀክቶችና ለመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ከጽ/ቤቱ በአነስተኛ ወለድ የሚሰጥ የረዥም ጊዜ ብድር ነው።
3. "ተበዳሪ ወይም ተበዳሪዎች" ማለት የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ድርጅት/ድርጅቶች ወይም የመስኖ የህብረት ሥራ ማህበር/ማህበራት ነው።
4. "የሚመለከተዉ የክልል መንግሥት ማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግሥት ዕውቅና የተሰጣቸውን ዘጠኝ የክልል መስተዳድሮችን ሲሆን፣ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል።

Archive
Office of the Water Resources Development Fund